### "ወጪውን ለመክፈል ባልችልስ?"

የመድን ዋስትና የትብብር ክፍያዎችን፣ የጋራ የመድን ዋስትና ክፍያን ወይም ተቀናሾችን መክፈል ባለመቻልዎ የተሰና ቤተሰብዎ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎት ማግኘት አይከለከልም። የሚሰጥዎትን ቅጽ መሙላትዎ መክፈል መቻልዎን ወይም አለመቻልዎን ይወስናል። ለእነዚህ ወጪዎች መክፈል እንደሚችሉ ከወሰንን፣ ክፍያዎቹን ሙሉ በሙሉ የመክፈል ኃላፊነት ይኖርብዎታል። የእርስዎ FRC እና አገልግሎት ሰጪ በዚህ ሂደት ውስጥ ያግዙዎታል።

በቤተሰቡ ገቢ ወይም ወጪዎች ላይ በማንኛውም ጊዜ ለውጥ በሚኖርበት ጊዜ ቤተሰቦች የመድን ዋስትና የትብብር ክፍያዎችን፣ የጋራ የመድን ዋስትና ክፍያን፣ ተቀናሾችን ወይም ወርኃዊ የቤተሰብ ክፍያዎችን መክፈል ስለመቻላቸው የተሰጠው ውሳኔ በድጋሚ ታይቶ እንዲወሰንላቸው ሊጠይቁ ይችላሉ።

አንድ ቤተሰብ የመድን ዋስትና የትብብር ክፍያዎችን፣ የጋራ የመድን ዋስትና ክፍያን፣ ተቀናሾችን ወይም ወርኃዊ ክፍያዎችን ለ90 ቀናት ሳይከፈል ከቀረ፣ በ EI ፕሮግራም ሥር የክፍያ ዕቅድ እስከሚዘጋጅ ድረስ የ IFSP አገልግሎቶችን ሊያቋርጥ ይችላል።

### *"ያለኝ የመድን ዋስትና የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶችን የሚሸፍን መስሎኝ ነበር።"*

አንዳንድ የጤና መድን ዋስትና ዕቅዶች የ EI አገልግሎቶችን የሚሸፍኑ ሲሆን አንዳንዶቹ ግን አይሸፍኑም። ለልጅዎ የ IFSP አገልግሎቶች ቤተሰብዎ በወጪ ላይ የሚሳተፍ ከሆነ፣ ያንን በተመለከተ የ EI ፕሮግራም ከእርስዎ ጋር በግል ይሰራል። የቤተሰብ የወጪ ተሳትፎ (FCP) ሁሉም ብቁ የሆኑ ልጆች አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ለማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።

### ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች?

እርስዎ የሚጠቀሙት የጨቅላነት የድጋፍ አገልግሎት(EI) ፕሮግራም የፕሮግራም ዳይሬክተር የቤተሰብ የወጪ ተሳትፎ (FCP)ን ወይም የጨቅላነት የድጋፍ አገልግሎቶችን በተመለከተ የሚኖርዎትን ማናቸውንም ጥያቄዎች መመለስ መቻል አለበት።



የእርስዎ የቤተሰብ መረጃ አስተባባሪ (FRC)
የሚከተለው ነው:-

ስልክ:-______________________________

ፕሮግራም:-___________________________

# የዋሽንግተን የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች

## የቤተሰብ የወጪ ተሳትፎ (FCP)

Department of Early Learning
Early Support for Infants and Toddlers (ESIT)
P.O. Box 40970
Olympia, WA 98504-0970
ስልክ:- 360.725.3500

DEL 11-019d (8/13)

# የዋሽንግተን የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ (EI) አገልግሎቶች

### *“የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎት (EI) ፕሮግራም ምን ያህል ወጪ ያስወጣል?”*

የልጅዎ የ EI አገልግሎቶች ምን ያህል ወጪ እንደሚያስወጡ አስቀድሞ መገመት የሚቻልበት ምንም መንገድ የለም። ከእርስዎ ጋር ተነጋግረን ቤተሰብዎ በጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎት ላይ በመሳተፉ በልጅዎ እና በቤተሰብዎ ላይ ሊያይዋቸው የሚፈልጓቸውን ለውጦች እስከምንወስን ድረስ ማወቅ አንችልም። ልጅዎ እና እርስዎ የሚያገኟቸው አገልግሎቶች ቤተሰብዎ ቅድሚያ በሚሰጣቸው ነገሮች፣ ሐብቶች፣ አሳሳቢ ነገሮች እና በልጅዎ ፍላጎቶች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። እነዚህም በእርስዎ እና ከእርስዎ ጋር አብረው በሚሰራው ቡድን ይወሰናሉ። የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች ለእያንዳንዱ ልጅ እና ቤተሰብ በግል የሚሰጡ ናቸው።



### *አገልግሎቶቹን ለማግኘት ወጪ ያስወጣል?*

የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች የትምህርት ሕግ (IDEA) ክፍል ሐ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች (EI) እንዴት እንደሚሰጡ የሚመራ የፌዴራል ሕግ ነው። IDEA ለአንዳንድ የ EI አገልግሎቶች የቤተሰብ ወጪ ተሳትፎን (FCP)ን ይፈቅዳል። FCP የአንድን ቤተሰብ የመንግስት ወይም የግል የመድን ዋስትና መጠቀምን ያካትታል። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ FCP የቤተሰብ ክፍያዎችንም ሊያካትት ይችላል።

### *“አገልግሎቶች ነጻ መስለውኝ ነበር።”*

የ IDEA ክፍል ሐ <u>አንዳንድ</u> የ EI አገልግሎቶች እርስዎ ምንም ወጪ ሳያወጡ እንዲሰጡ ያዛል። እነዚህ ተግባራት የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- ልጅን መፈለግ (ለEI ብቁ ሊሆኑ የሚችሉ ልጆችን ተዘዋውሮ መፈለግ)።
- ግምገማ እና ምዘና (አንድ ልጅ ለ EI ብቁ መሆኑን ለመወሰን)።
- የአገልግሎት ማስተባበር(ለቤተሰቦች መረጃን የሚፈልጉ ተግባራት)።
- በግል የሚሰጥ የቤተሰብ አገልግሎት ዕቅድ (IFSP) ዝግጅት እና ክለሳዎች።
- የወላጅ መብቶች (የሥነ-ስርዓት ጥበቃዎች እና መደበኛ የክስ መስማት ሂደት በመባል ይታወቃሉ)።

### *“ወጪ ሊኖር እንደሚችል በምን አውቃለሁ?”*

እንዲሞሉ የሚጠየቁት ቅጽ ለአገልግሎቶች ማንኛውም አይነት ወጪ የሚኖር ከሆነ፣ ያንን ለመወሰን ይረዳዎታል። በቅጹ ላይ የእርስዎን የመንግስት ወይም የግል የመድን ዋስትና ለመጠቀም ፈቃድ ከሰጡ እና የመድን ዋስትና የትብብር ክፍያዎችን፣ የጋራ የመድን ዋስትና ክፍያን፣ እና ተቀናሾችን ለመክፈል ከተስማሙ ማንኛውንም የፋይናንስ መረጃ መስጠት አይኖርብዎትም። የመድን ዋስትና የትብብር ክፍያዎችን፣ የጋራ የመድን ዋስትና ክፍያን፣ ተቀናሾችን ወይም ወርኃዊ ክፍያዎችዎን ለመክፈል የማይችሉ ከመሰለዎት ለአገልግሎቶች ማንኛውም ወጪ መኖር አለመኖሩን ለመወሰን የፋይናንስ መረጃ መቅረብ አለበት።

### *“ስለገቢዬ ወይም ስለጤና የመድን ዋስትናዬ መረጃ ለመስጠት ካልፈለግኩኝስ?”*

ቤተሰቦች ስለገቢያቸው መረጃ ያለመስጠት ወይም ፕሮግራሙ የእነርሱን የመንግስትም ሆነ የግል የጤና መድን ዋስትና እንዳያስከፍል የመምረጥ መብት አላቸው። ገቢን የሚመለከት መረጃ ላለመስጠት ከመረጡ፣ ለሜዲኬይድ ያመልክቱ (ብቁ ከሆኑ)፣ ወይም ፕሮግራሙ የመድን ዋስትናዎን እንዲያስከፍል ይምረጡ፣ በቤተሰብዎ መጠን እና ገቢ መሰረት የቤተሰብ የወጪ ተሳትፎ (FCP) ለሚመለከታቸው አገልግሎቶች ወርኃዊ የቤተሰብ ክፍያ እንዲከፍሉ ይመዘናሉ።

ቤተሰብ ሊያወጣቸው ስለሚችሉ ወጪዎች ይበልጥ ዝርዝር መረጃ የቤተሰብ መረጃ አስተባባሪ (FRC) በሚሰጥዎ በሥርዓት ክፍያዎች ፖሊሲ ውስጥ ይገኛል።

**የቤተሰብ የገቢ እና ወጪ መረጃ በሚስጥር የሚያዝ ነው። እርሰዎ ፈቃድዎን በጽሁፍ ሳይሰጡ ለሌላ ለማንኛውም ፕሮግራም (የመንግስትም ሆነ የግል) አይሰጥም።**

### *“ወደሌላ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎት የተዘዋወርኩ ወይም የተሸጋገርኩ እንደሆነስ?”*

ለአዲሱ የ EI ፕሮግራም ስለቤተሰብዎ መጠን፣ ገቢ እና የመድን ዋስትና መረጃ መስጠት አለብዎ እንዲሁም ለአዲሱ ፕሮግራም ለመክፈል እንዲረዳዎ የእርስዎን የመንግስት ወይም የግል የመድን ዋስትና ለመጠቀም ፈቃድ መስጠት አለብዎ።